የኢትዮጵያ ክፍለሀገራት ሕብረት
Ethiopian Kifle-Hagerat Hibret
www.ethiopianhibret.com
ethiopianhibret@gmail.com

# የተሳካ ስብሰባ!

የካቲት ፳፭ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓም (04-03-2018)

ከስድስት ወራት በፊት (ጁላይ 6 ቀን 2017) በሲያትል ከተማ በአምስት የኢትዮጵያ ክፍላተ-አገር ማኅበራት፣ ማለትም በጎንደር ኅብረት ለኢትዮጵያ አንድነት፣ በሸዋ ሁለገብ ማኅበር፣ በወሎ የኢትዮጵያ ውርስና ቅርስ ማኅበር፣ በጎጃም ዓለም አቀፍ ማኅበርና በሲዳሞ ማኅበረሰብ ተመሥርቶ አሁን ሌሎቹንም ክፍለ-አገሮች እያጠቃለለ የመጣው የኢትዮጵያ ክፍላተ-አገር ኅብረት የመጀመሪያውን ስብሰባ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የካቲት ፲፰ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ/ም (25-02-2018) ብዙ ታዳሚ በተሣተፈበት መልኩ በተሳካ ሁኔታ አጠናቋል።

የስብሰባውን ሂደት በቀጥታ ዓባይ ሚዲያ በቦታው ተገኝቶ የዘገበው ሲሆን ኢትዮጵያውያን በያሉበት ስብሰባውን እንዲከታተሉ ዕድሉን ፈጥሮላቸዋል።በዚህ የጋዜጠኝነትን ሥነ-ምግባር ባከበረ፣ ወገንተኝነት ባልተጠናወተው፣ በተሟላ የዜና አቀራረብ፣ በባለሙያዎቹ ችሎታና ቀና ተሳትፎ ኅብረቱ ለዓባይ ሚዲያ ተቋም በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ምስጋናውን እያቀረበ፣የኢትዮጵያ ጉዳይ በሚነሳበትና በሚቀርብበት ቦታና ጊዜ ሁሉ እየተገኙ የባለሙያ ግዴታቸውን በመወጣታቸው ያለውን አክብሮትና ምስጋና ሊገልጽላቸው ይወዳል። ይህ አሠራራቸውና የጋዜጠኝነት ሙያቸው እንዳይበረዝ አደራ እያለ፣ በያዛችሁበት ቀጥሉበት ይላል። ለሚያደርጉት ጥረት ከጎናቸው እንደሚቆምና ድጋፉን እንደማይነሳቸው ሊገልጽላቸው ይወዳል።

"የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ላይ ያስታውቃል" እንዲሉ! የክፍላተ-አገር ኅብረት አወቃቀርና ዓላማ እስከዛሬ ድረስ ከሚታወቁት አደረጃጀቶች የተለየና የአገራችንን ችግር በተለይም ላለፉት አምሳ ዓመታት ተዘርቶ ባለፉት ፳፯ ዓመታት ጎምርቶ አገር አፍራሽ፣ ሕዝብ አጫራሽ የሆነው የጎሣ ፖለቲካ የጠነሰሰውን መርዝ ለማምከንና የቀየሰውን ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ- አንድነት የሆነውን የጥፋት መንገድ አስወግዶ፣ የተደፈረው የኢትዮጵያ ዳር ድንበርና አንድነቷ ተከብሮ እንዲኖር፣ የአገራችን የወደፊት የውስጥ አስተዳደራዊ አደረጃጀት ሕዝብ መክሮ የሚበጀውን መወሰን እስከሚችል ድረስ የሕዝቧን አኗኗርና አሠፋፈር መሠረት ያደረገውንና ቅድመ-ሕወሓት/ኢሕአዴግ የነበርውን የክፍላተ-አገር ወሰን መከተሉ አስፈላጊ ነው። የክፍላተ-አገር ማኅበራችን ሕዝብ በጎሣው፣ በሚናገረው ቋንቋ፣ በእምነቱና በባኅሉ ሳይፈረጅ፣ በፈለገበት ቦታ ሠርቶና ሃብት አፍርቶ የመኖር የዜግነትና የሰብዓዊ መብቱ ተከብሮለት፣ በሚኖርበት አካባቢም በፖለቲካው፣ኤኮኖሚውና ማኅበረሰብዓዊ ጉዳዮች ላይ እኩል ተሣትፎ እንዲኖረው በዴሞክራሲያዊ አሠራር የከባቢ እራስን የማስተዳደር ሥርዓት እንዲሰፍን ለማድረግ የሚታገል አገር-አቀፍ ድርጅት ነው። እያንዳንዱ ማኅበር የአካባቢውን ልማትና እድገት በሚመለከት አስተዋጽዖ ለማድረግ የተቋቋመ ቢሆንም ልማትና እድገት የሚታሰበው አገርና ሰላም ሲኖር በመሆኑ ለዚያ ቅድሚያ ይሰጣል።

የኢትዮጵያ ክፍላተ-አገር ኅብረትን እንደ አዲስ አማራጭ የሚመለከቱና ተስፋ የጣሉበት ብዙ ናቸው። ጥቂቶች ደግሞ የተሰለፉበትን መንገድና የሚከተሉትን ድርጅት የሚቀናቀንና ደጋፊ አልባ ያደርገናል በሚል ስጋት የኅብረቱን ምሥረታ ከጧቱ ጀምረው በመቃወም የሃሰት ዘመቻ ከማካሄድ አለመቦዘናቸው በዚህ ስብሰባ ወቅትም የተገነዘብነው አሳዛኝ ክስተት ነበር። ያም ሆኖ ግን እውነት እንደጀንበር እየገለጠ መምጣቱ አይቀርምና አፍራሽ ዘመቻውን ተቋቁመው፣ የክረምቱ ብርድ ሳያግዳቸው በስብሰባው ላይ የተገኙት አገር-ወዳዶች ቁጥር ቀላል አልነበረም። ላደረጉት ድጋፍና ንቁ ተሳትፎ የኢትዮጵያ ክፍላተ-አገር ኅብረት ምስጋናውንና አክብሮቱን ይገልጻል።

ስብሰባውን ለማዘጋጀት ከተመደበው የሰው ኃይልና የጊዜ እጥረት፣ ከተደረገበትም አፍራሽ ዘመቻ አንጻር ሲታይ፣ አዳራሹ ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ አልፎ-አልፎ የወንበር ክፍተት ቢታይም የተገኘው ተካፋይ ቁጥር ቀላል አልነበረም።

የክፍላተ-አገር ም/ሊቀ መንበር የሆኑት አቶ አሰግድ ሸነገለኝ እንኳን ደኅና መጣችሁ በማለት ንግግር ካደረጉ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተ-ክርስቲያን የእምነት አባቶች በአቡነ ፊሊጶስ መሪነት ተገኝተው ስብሰባውን ባርከው ከፍተዋል።

የኅብረቱ አባል ማኅበራት ተጠሪዎችና አስተባባሪዎች በየተራ ስለሚያደርጉት እንቅስቃሴና ስለ ኅብረቱ ጥቅም አጭር ማብራሪያ ሰጥተዋል። የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሠራዊት አባላት ማኅበር ተወካዮችም በቦታው በመገኘት የበኩላቸውን ድጋፍና መልእክት አስተላልፈዋል፤በውይይቱም ወቅት አሳባቸውን የሰጡ ሲሆን ለወደፊቱ ከኅብረቱ ጎን እንደሚሠለፉ ቃል ገብተዋል።

የኅብረቱ አባል የሆኑት ምሑራን በተለያዩ እርእሶች፤ ማለትም፣

1. 'ድምፅ-አልባው ጭፍጨፋ (silent genocide)'፣ በዶ/ር መሐሪ ፍስሃ (ከአየርላንድ በስካይፕ መስመር)፤

2. 'የሲቪክ ማኅበራት ጥቅምና ድርሻ ከፖለቲካ ድርጅቶች አንጻር'፣ በዶ/ር ብርሃኑ አበጋዝ፣

3. 'ከዛጉዌ /ላሊበላ/ መንግሥት በኋላ የኢትዮጵያ አመሠራረት አጭር ታሪክ'፣ በፕ/ር ዳንኤል ክንዴ፣

4. 'የክፍላተ-አገር አደረጃጀት ጥቅምና ታሪካዊ ድርሻ'፣ በፐ/ር. ዓለምአንተ ገ/ሥላሴ፣ ቀርበው በጽሑፍ ያዘጋጁቸውን ጥናታዊ መልእክቶች በቃል አቅርበዋል። *(በቅርብ ጊዜ ውስጥ እነኝህ ምሑራን ያቀረቧቸው ጥናታዊ ጽሑፎች በኅብረቱ ድረ-ገጽ ላይ ይቀርባሉ።)*

የምሑራኑ ትንተና ከቀረበ በኋላ ዶ/ር አምባቸው ወረታ የማጠቃለያ አስተያየትና ምክር ሰጥተው መድረኩ ለውይይት ተከፈፍቶ ታዳሚዎች በቀረቡት ትንታኔዎች ላይ ጥያቄና አስተያየቶቻቸውን በማቅረብ ሠፋ ያለ ውይይት ተካሂዷል። ታዳሚዎቹ ለኅብረቱ የወደፊት እድገት የሚረዱ ምክሮችን በመሰንዘር ድጋፋቸውን በመግለጽና በአባል ማኅበራት ውስጥ ለመሣተፍ ስምና አድራሻቸውን በመስጠት ተብብራቸውን አሳይተዋል። ከአምስት ሰዓት በላይ የፈጀውን ስብሰባ ባርከው የከፈቱት የእምነት አባቶች በውይይቱ ወቅት ሰፊ ተሣትፎ በማድረግ አሳብና ምክር ሰንዝረዋል፤በመጨረሻውም ባርከው የከፈቱትን ስብሰባ መርቀው አሳርገዋል።

ስብሰባው እንዲሳካ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ላስተባበሩት፣ እንግዶቹን ላስተናገዱት በተለይም ሴቶች የኅብረቱ አባላትና ደጋፊዎች ከፍተኛ አድናቆትና ምስጋና ይገባቸዋል።

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነፃነት ለዘላለም ትኖራለች!

የኢትዮጵያ ክፍላተ-አገር ኅብረት